ለአሐዱ ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማና ምርጫ መሥፈርቶችን ለማሳወቅ የወጣ ማስታወቂያ

አሐዱ ባንክ አ.ማ ጥቅምት 28 ቀን 2019 ዓ/ም በአዲስ ኮንቬንሽን የስብሰባ ማዕከል በሚያካሒደው 5ኛው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ለቀጣዩ ሦስት የሥራ ዓመታት ባንኩን የሚያገለግሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይመርጣል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 እና SBB/89/2024 እንዲሁም በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አፈጻጸም ደንብ ቁጥር 2/2018 አንቀጽ 12.1 መሠረት፣ ዕጩ የሚሆኑ አባላትን ለማዘጋጀት እንድትችሉ የቦርድ አባል ሆኖ ለመጠቆም መሟላት ያለባቸውን መሥፈርቶች እናሳውቃለን።

ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት መሥፈርቶች

1. በባንኪንግ፣ በአካውንቲንግ፣ በኦዲት፣ በፋይናንስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፣ በዲጂታል ባንኪንግ ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ እውቅና ካለው ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በሙያው ቢያንስ የ 7 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣
2. ቢያንስ ለሁለት ዓመት የባንኩ ባለአክሲዮን የነበረ እና የሌላ ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ
3. የቦርድ አባል ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነና በዳይሬክተርነት ለማገልገል በቂ ጊዜ ያለው፣
4. በሌላ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ ወይም ከ 4 በላይ በሆኑ በየትኛውም ሌላ ተቋም ውስጥ ዳይሬክተር ያልሆነ፣
5. ከዚህ በፊት ከመንግሥት መረጃን በመደበቅ፣ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት፣ ተቆጣጣሪ አካላት የሚያስቀምጡትን መሥፈርቶች ባለማሟላት እና መሰል ድርጊቶች ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፣
6. ከዚህ በፊት በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች ኃላፊነቶች ተመድቦ ሲሠራ በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር ከኃላፊነቱ በተያያዘ ወይም ማንኛውንም ሌላ ሁኔታ ውስጥ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት ወይም በውንብድና ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፣
7. ከባንኩ ጋር ምንም ዓይነት የጥቅም ግጭት የሌለው፣
8. ከየትኛውም ባንክ ብድር ወስዶ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተበላሸ ብድር የሌለው፣
9. ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ባለቤት በሆነበት ድርጅት፣ የመክሰር ሒደት ያላስጀመረ ወይም መክሰሩ ያልተወሰነበት፣ ንብረት ያልተወረሰበትና፣ ንብረቱ በመክሰር ውሳኔ መሠረት እንዲተዳደር ያልተደረገበት ወይም የባንክ ብድር ለመክፈል ባለመቻሉ ንብረቱ በዕዳ ማስመለሻነት ያልተሸጠበት፣
10. በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ ለክፍያ ሰጥቶ የባንክ ሒሳቡ ያልተዘጋበት እና
11. ሌሎች ጸባቢነት ባላቸው ሕጎች እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጡ መመሪያዎች ላይ የተዘረዘሩ መመዘኛዎችን የሚያሟላ
12. በወንድ ጾታ የተገለጠው መሥፈርት ለሴት አመልካቾችም ተፈጻሚነት አለው።

ማሳሰቢያ

1. በባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት የሚመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር 12 ነው።
2. ከአጠቃላዩ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት 1/3ኛ የቦርድ አባላት ሥራ ላይ ባለው ቦርድ ተጠቁመው በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡት ገለልተኛ ዳይሬክተሮች (INDEPENDENT DIRECTORS) ናቸው። ባንካችን ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች ስለሌሉት ቀሪዎቹ ዳይሬክተሮች በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይመረጣሉ።
3. ከገለልተኛ ቦርድ አባላት ዕጩዎች ጥቆማ በስተቀር የቀሪዎቹ አባላት ጥቆማ የሚካሔደው እና የሁሉም የቦርድ አባላት ምርጫ የሚደረገው በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ዕለት ነው።
4. በዕጩነት ከተጠቆሙት ውስጥ ቢያንስ 2 ሴቶች የቦርድ አባል ሆነው መመረጥ አለባቸው።
5. በምርጫው ዕለት 5 አባላት ያሉት የአስመራጭ ኮሚቴ ይመረጣል። የኮሚቴው አባል የሆነ ሰው ለቦርድ አባልነት ሊመረጥ አይችልም።
6. ከላይ የተጠቀሱት የጥቆማና ምርጫ መሥፈርቶች ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ለሚወክለው የተፈጥሮ ሰውም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል።
7. አንድ ባለአክሲዮን ራሱን በዕጩነት መጠቆም ይችላል።
8. የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ የሙያ እና የጾታ ስብጥርን ማረጋገጥ አለበት ።
9. በጥቆማ ወቅት የጠቋሚዎች ስምና የአክሲዮን መጠን መገለጽ አለበት።
10. አንድ ባለአክሲዮን የሚጠቁመውን ዕጩ በተመለከተ አጭር የትምህርትና የሥራ ልምድ ማብራሪያ መስጠት አለበት።
11. የቦርድ አባላትና የባንኩ ሠራተኞች ባለአክሲዮኖችን ወክለው ድምፅ መስጠት አይችሉም።
12. የምርጫው ሒደት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አፈጻጸም ደንብ ቁጥር 2/2018ን መሠረት በማድረግ ይፈጸማል። የአሠራር ደንቡን ከባንኩ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

የማህበሩ ጸሀፊ
አሐዱ ባንክ አ.ማ